# የትግሉ ነው ሕይወቴ

ለዘመናት በጭቆና ማጥ
በግፍ ሰንሰለት ታስሬ
መብቴን ላስከብር
ጨቋኙን ልሽር
ተነስቻለሁ ዛሬ
ይኸው ታጥቄያለሁ ዛሬ

ባንድ እንደሚነሳ
የሕዝብ ወገን ሁሉ
ለማያጠራጥር ድሉ
ፍጹም ነው እምነቴ
የትግል ነው ሕይወቴ
ልጓዝ በድል ጎዳና
በተሰዉት ጓዶች ፋና

የግፍ ሥርዓትን ጭቆና
የዘረኞችንም ሴራ
እስከማጠፋ ትግሌን ልቀጥል
በጨቋኞች ላልገዛ
ቃልኪዳኔንም ላልረሳ

ረሃብ አይፈታኝም
ችግር አይገታኛም
ከትግሉ አያግደኛም
ፍጹም ነው እምነቴ
የትግሉ ነው ሕይወቴ
ልጓዝ በድል ጎዳና
በተሰዉት ጓዶች ፋና

የሕዝብ ታማኝ አገልጋይ ነኝ
የማልበገር ወታደር
ብረት አነሳሁ
ለትግል ተናሳሁ
ጠላት ይፍራ ይሸበር
ያድርባይ ቅስሙ ይሰበር

ቢወቀጥ አጥንቴ
ቢንቆረቆር ደሜ
ላዲስ ሥርዓት ልምላሜ
ፍጹም ነው ዕምነቴ
የትግሉ ነው ሕይወቴ
ልጓዝ በድል ጎዳና
በተሰዉት ጓዶች ፋና